# <u>በሽታውን ያላወቀ መድኃኒት የለውም</u>

## <u>ከ አብርሃም ያየህ</u>

በሽታን ለማስወገድ አራት ነገሮች መደረግ አለበት።

1. በሽታን በትክክል ለይቶ ማወቅ።
2. በሽታው በትክክል ከታወቀ በኋላ ትክክኛውን መድሃኒት ፈልጎ ማግኘት።
3. መድሃኒቱ ስለተገኘ ብቻ ፈዋሽ ሊሆን ስለማይችል የተገኘው መድሃኒት ሐኪም በሚያዘው መሠረት በትክክል መውሰድ።
4. በህክምና የተወገደውን በሽታ ተመልሶ እንዳይመጣ  አስፈላጊውን መከላከል ማድረግና ለበሽታው መንስኤ ከሆኑ ነገሮች ራስን ማግለል ይጠይቃል።

የአገራችን ምሁራን በሽታ በሽታችንን ለይተው ለማወቅ ያለመቻላቸው ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም።

የአገራችንና የህዝባችን በሽታ ማሌሊት ነው። የማሌሊት ወረርሺኝ ለማስወገድም ትክክለኛው መድኃኒት በእጃችን አለ። አሁን የሚቀረን ታማሚው ህዝባችን መድኃኒቱን የሚጠቀምበት መንገድ ማመላከትና እንደገና በበሽታው እንዳይለከፍ ራሱን የሚከላከልበት ዘዴ መጠቆም ብቻ ነው።

አንዳንድ በቅርቡ ብቅ ያሉ ምሁራን ተብየዎች ዋና ችግር (በሽታ) ወያኔ በፈጠረው ግርግር ሳቢያ ተጠቅመን ኢትዮጵያን የአሰብ ወደብ ባሌቤት እናድርግ የሚል በሽታ ነው። በዚህ መልክ የኢትዮጵያ በሽታ የሚፈወሰው ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብ በሚባል መድኃኒት ስትታከም ብቻ መሆኑ ነው። ይህንን መፈወሻ መድሃኒት የሚያገኝልን የህክምና ተቋም ደግሞ የመለስ ዜናዊ ማሌሊት ሊሆን ነው። በሽታን በበሽታ ማከም ይቻል ይሆን?

በሐኪሙ በመለስ ዜናዊና በግብረአበሮቹ የማሌሊት አስታማሚዎች ጭንቅላት የሚሽከረከረው አጀንዳ ምንነት በቅርቡ በሌላ ጽሁፍ እመለስበታለሁ። በቅድሚያ ግን አሰብ ስለሚባለው መድሃኒት ለመተቸት እወዳለሁ።

ኢትዮጵያዊ እንደመሆኔና፣ የኢትዮጵያ ጥቅም የኔም ጥቅም በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብ ብቻ ሳይሆን የምፅዋም፣ የጁቡቲም፣ የበርበራም፣ የሌሎች ወደቦችም ባለቤት ብትሆንልኝ በደስታ ለመፈንደቅ በእጅጉ ዝግጁ ነኝ። የኔ ትኩረት፣ ኢትዮጵያ በኤርትራ መሬት ለሰላሳ ዓመታት በዘለቀው ዘመቻና አሁን ለምትገኝበት ድህነትና ጉስቁልና የዳረጋትን አእላፍ ህይወትና ገንዘብ ስታጠፋ ለወደብ ፍለጋ ብቻ ነው? ወይስ በኤርትራ ምድር የሚኖረውንም ህዝብ ህዝቤ ነውና አይሂድብኝ ስትል ነው4 የሚለውን ጥያቄ ለውይይት ለማቅረብ ነው።

የኤርትራ ነፃነት፣ በነመለስ ዜናዊ ቃለ ቡራኬ ተጠናቅቆ፤ ኤርትራ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል በመሆን እውቅና ስታገኝ፤ የኤርትራ ጉዳይ አሰብን አጠቃልሎ እንዳበቃለት ያለመገንዘብ ሞኝነት ወይም የዋህነት ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ፣ በዓለም ህብረተሰብ መድረክ ኢትዮጵያን ወክሎ የሚደራደረው ወያኔ፣ «አሰብ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም» በማለት በተደጋጋሚ አቋሙን ግልፅ ማድረጉን እየታወቀ ሳለ፣ አንዳንድ  ኢትዮጵያዊያኖች በአየር ላይ እየተንሳፈፉ አሰብን የኢትዮጵያ ወደብ እናደርጋለን እያሉ ሲባክኑ መታየታቸው ነው። ከዚህ የበለጠ ሞኝነት (የዋህነት ትንሽ ለስለስ ይላል) ሌላ ምን ይኖራል4

የአሰብ ወደብ ተሟጋቾች «ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ፣ ጅግራ ይሏታል» እንዲሉ፣ አሰብ የኢትዮጵያ የሚሆነው አፋሮች ኢትዮጵያዊያን ስለሆኑ ነው የሚል ጥሬ ክርክር ያነሳሉ። በኢትዮጵያ የተረሱ ከምንላቸው ህዝቦች አንዱ የሆነው የአፋር ህዛባችን፣ የአሰብ ወደብ ለመጨበጥ እንዲያስችለን ሲባል ብቻ ልናቆላምጠው ብንሞክር፣ ትርፉ መሳቂያ መሆን ብቻ አይሆንም? በኢትዮጵያ፣ በኤርትራና በጂቡቲ የሚኖሩ አፋሮች አንድ ህዝብ ነን ብለው የሚያምኑ ናቸው። ታዲያ አፋር የሰፈረበት ሁሉ የኛ እንዲሆን የምንሻ ከሆነ፣ ትኩረታችን ወደ ጂቡቲም ማድረግ እንችል ይሆን? ትናንት፣ የኤርትራ ህዝብ ህዝባችን ነው ብለን፣ ያለ የሌለ ቅርሳችንን አፍስሰንና በሺዎች የሚቆጠሩ የውድ ዜጎቻችን ህይወት ሰውተን፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራዊያኖችም ጨፍጭፈንና እኛም ተጨፍጭፈንሽ ዛሬ ለወደብ ስንል ቆንጥረን ህዝባችን አፋር ብቻ ነው እንበል?

የዳኘው ምኒልክ ህጋዊ አልጋወራሽ የሆነው ኢያሱ፣ ከአፋር ጉብል ልጅ ወልዶ የአፋር ደም ከንጉሣዊያን ደም ቀላቀለው። የአፋር ኢትዮጵያዊነት ከዘላን መንደር ወጥቶ በኢትዮጵያ ቤተመንግሥት እንዳይገኝ ስንል፣ በኢያሱ ላይ ጭራ ቀጥለን፣ ኢያሱ የተቀበረበትን ስፍራ እንኳ ለማወቅ ሳንሻ ፀጥ ብለን ኖርን። ዛሬ አሰብ ለምትባል ጉብል ስንል፣ አፋር አፋርየ ብለን ብናቅራራ፣ የሌላው ቢቀር፣ የአፋሮች መሳቂያ አንሆንም?

ከዚሁ ከአሰብ አሰብየ መዝሙር ሳልወጣ መጥቀስ የሚገባኝ ቁምነገር አለ። ወያኔ ህልሙም ሆነ ራዕዩ ለትግራይና ለትግራይ ብቻ መሆኑን ለማሳመን ብዙ መኳተን ያለብኝ አይመስለኝም። የአሰብ ወደብ ደግሞ ጥንትም ሆነ ዛሬ ለትግራይ አመቺ የባህር በር አይደለም። ለትግራይ አመቺ በር የምፅዋ ወደብ ነው። ስለሆነም የወያኔ ጥረት ለትግራይ ልማትና እድገት የሚጠቅመውን የምፅዋ ወደብ ለማስከፈት፣ በኤርትራ የቀድሞ ወዳጁን ሻዕቢያን አስወግዶ፣ የራሱ አጋር የሆነ አዲስ መንግሥት ማቆም መሆኑን በጥሞና መገንዘብ ያስፈልጋል።

ለመሆኑ ይህ አሰብን በማስመልከት የተነሳው ጫጫታ ከየት መነጨ? ካሁን በፊት ደርግም ሆነ ወያኔ ዴሞክራሲ ያስፍኑ፣ ሰብአዊ መብት ያክብሩ እያልን ስናለቅስ በመድረክ ያልታዩ አንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን ሳይቀሩ፣ አሁን በድንገት ብቅ ብለው፣ ያዙን ልቀቁን አስከሚሉ ድረስ፣ በአሰቡ ጥያቄ ለመረባረብ የበቁት በማን ግፊት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ከየቦታው ይቀርባሉ። የማውቀውን ላብራራ።

የአሰብ ወደብ ጥያቄ በኢትዮጵያዊያን ጓዳ የዊስኪና የካቲካላ ማወራረጃ እንዲሆን ያደረገው ወያኔ ራሱ ነው። ወያኔ ከኤርትራ ጋር ለሚያስኬደው ጦርነት የኢትዮጵያዊያን ድጋፍ በእጅጉ ያስፈልገው ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ከወያኔ ጋር በፍቅር ድብን ብሎ ድጋፉን እንደማይሰጠው ራሱ ወያኔ ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ የወያኔው «ባዶ ሦስት» ኢትዮጵያዊያንን አስጎምጅቶ ድጋፋቸውን የሚያስገኝበት ልብ የሚሰልብ ጉዳይ እንዲያፈላልግ ግዳጅ ተሰጠው። በአቃቂረኞች ዘንድ «ባዶ ሦስት» አንዳንዴም «አየር ባየር» በመባል የሚታወቀው የወያኔ የህቡእ ፕሮፓጋንዳ ዘርፍ ዋና ተግባር፣ ወያኔ በዜና ማሰራጫዎችና በመድረክ ሊገልፃቸው የማይፈልጋቸውን የማዘናጊያ ጉዳዮች እውነት አስመስሎ በህዝብ ዘንድ የማስረፅ ተልእኮ ያለው ዘርፍ ነው።

በዚህ ረገድ «ባዶ ሦስት» የኢትዮጵያውያንን ልብ ሰልቦ ድጋፍ ያስገኛል ብሎ ያመነበት ጉዳይ <u>«ዋናው ዓላማችን አሰብን መልሰን ለማምጣት ነው»</u> የሚል ወሬ ለህዝብ ማሰራጨት ሆኖ ተገኘ። በታዋቂው የማሌሊት ዲያቆንና፣ የመለስ ቀኝ እጅ፣ የዋልታ ኢንፎርመሽን ሰርቪስ ሃላፊ በሆነው በነጋሽ ተክሉ የተመራው፣ ይህ የልብ መስለብ ሥራ፣ በሚገባ የሠራና በርካታ ኢትዮጵያዊያንን አፍዝዞ ያደነዘዘ አስደናቂ የሥራ ውጤት ነው። ወያኔን ባልወድም ቅሉ፣ ከሞኛሞኞች ኢትዮጵያዊያኖች (አብዛኞቹ አማሮች) ይልቅ፣ ወያኔ ቢያንስ ለህልውናው ጠንክሮ የሚሠራና፣ እርስ በርሱ እየተባላ ጊዜውን የማያባክን መሆኑን በትክክል መናገር እችላለሁ። የሚቀጥለው የወያኔው «እፎይታ» መፅሄት እትም «አብርሃም ያየህ የአማራውን ህዝብ ሞኝ ነው አለ» በሚል ርዕስ ሰፊ ሀተታ ይዞ እንደሚወጣ ተስፋ አደርጋለሁ። ቃሉን የተጠቀምኩበት፣ አንጀት አራሹ የጦቢያ ብዕረኛ ፀጋይ ገብረ መድህን አርአያ «ሞኞች ነን» ሲል ካቀረበው ፅሁፍ ተውሸ መሆኑን ይታወቅልኝ።

ከተነሳሁበት ርዕሰ ነገር ለመራቅ ባፈልግም ቅሉ፣ ባሁኑ ጊዜ የወያኔው «ባዶ ሦስት» እየመነዘረው ያለው ወሬ ደግሞ፣ «አማራውና ትግሬው ግምባር ፈጥሮ በሻዕቢያና በኦሮሞ ላይ ይዝመት። ኦሮሞንና ሻዕቢያን ካዳከምን በኋላ የትግራይ ህዝብ በአማራ ላይ ለፈፀመው በደል ይቅርታ ይጠይቃል። የትግራይና የአማራ ህዝብ አንድ ዓይነት ህዝብ ነው።» የሚል መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁ። የወያኔ መንጠቆ በዚችም ቢያንስ አንዳንድ ደቃቃ አሳዎችን ይዛ ብቅ ብትል አያስገርመኝም።

ወደ አሰቡ ጉዳይ ልመለስ። የወያኔ አፍዝ አደንዝዝ ወሬ፣ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን በማታለል የወያኔ የጦርነት ነጋሪት እንዲጎስሙ ካስደረገ በኋላ፣ አንድ ችግር ገጠመው። ወያኔ ብዙ ሚልዮን ብር እያፈሰሰ ያደራጃቸው የሻዕቢያ ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የሚንሸራሸረውን የአሰብ ወደብ ጉዳይ አሳስቧቸው፤ ወያኔን አንቀው፣ «በአሰብ ጉዳይና፣ በአጠቃላይም በኤርትራ ሉዓላዊነት የመንግስታችሁ አቋም ምንድንነው?» ማለት ጀመሩ። ወያኔም፣ አሰብ የኤርትራ አካል መሆኗንና፣ በኤርትራ ሉአላዊነትም የአቋም ለውጥ እንደሌለ አስረገጠ። ኤርትራዊያኑም ይህንኑ በጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ እንዲሆንላቸው ሲጠይቁ፣ አቶ መለስ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ጥቂት

ዲፕሎማቶች ሰብስቦ፤ ኢትዮጵያ በአሰብም ሆነ በኤርትራ ሉአላዊነት ላይ ጥያቄ እንደሌላት ሲያበስር፣ የኤርትራዊያኑ ጭንቀት ሊወገድ ቻለ። ኤርትራዊያኑ የሰጉት «የኤርትራ የሉዓላዊነት ጉዳይ ለድርድር የሚቀርብ ከሆነ ኤርትራዊያንን እንዴት ለማደራጀት ይቻለናል?» የሚል ነው።

የኤርትራዊያን ተቃዋሚዎች ጭንቀት ሲረግብ፣ የሞኞቹ የአሰብ ተስፈኞች ጎራ በራስ ምታት ተበጠበጠ። በሽታውን በትክክል ያላወቀ ሰው ሲበጠበጥ ሊኖር የግድ አይደል? ብልጡ ወያኔ በትውልዱ አገር በትግራይ፣ በደርግ የተወረሰውን ቤት ለቀድሞ ባለንብረት ሲመልስ በዋናነት ያነጣጠረው ከትግራይ ውጭ የሚኖረው ህዝብም (በተለይ ያዲስ አበባው ተላሌ) ንብረቴ ይመለስልኛል ብሎ ይተባበረኛል በሚል ነበር። ከተመኘው ህዝብ አጥጋቢ ትብብር ለወያኔ ሲሰጥ እዚያው አዲስ አበባ ስለነበርኩ፣ እየተገረምኩ ስስቅ ነበር። ወያኔ አዲስ አበባ ገብቶ የተላላዎቹን ቅስም ሲሰብረው አንጀቴን አራሰው. በአሰቡ ጫጫታ ስደነቁር ከከረምኩ በኋላ፣ አሁንም ወያኔ ውሎ ይግባ አንጀቴን እያራሰው ነው። ወያኔን ባልወድም «ብራቮ ወያኔ» ብልለት የሚያንሰው አልመሰለኝም።

የአሰቡን ንትርክ ላጠቃልል። ኢትዮጵያ በኤርትራ ምድር ከወደቡ በላይ ሌላ ጠቃሚ ነገር ያስፈልጋታል። የኤርትራ ህዝብ። በኢትዮጵያ ምድር ስልጣን የጨበጠ ሁሉ፣ የኤርትራን ህዝብ በቀጠቀጠ ቁጥር፣ አብረን የምናጨበጭብና ድንጋይ የምናቀብል ከሆነ፣ የወደቀችውን አገራችን ጨርሳ እንድትጠፋ የወሰንን መሆን አለብን።

ወቅቱ የኤርትራን ፋይል እንደገና ከፍተን እንድንመረምር ያስገድደናል። የኤርትራ ፋይል ደግሞ ያለው በኤርትራ ህዝብ ስልጣን ስር ነው። አማራውንም፣ አፋሩንም፣ ኦሮሞውንም፣ ኦጋዴኑንም፣ ትግሬውንም ሆነ ሌላው በኤርትራ ህዝብ ላይ ያለውን አመለካከት በጥንቃቄ መመርመር አለበት። የበሽታችን መድኃኒት ረጋ ብለን በንጹህ ልቦና ከኤርትራዊያኑ ወገኖቻችን ጋር መወያየት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። ወያኔ የተባለ መቅሰፍት በኢትዮጵያ ቤተመንግሥት አስቀምጠን፣ በዓለም ህብረተሰብና በህግ ፊት የማናሸንፍበት ሙግት በማንሳት፣ ወርቃማውን ጊዜያችንን በከንቱ የምናባክን ከሆነ፣ እውነትም የጦቢያው ብዕረኛ ፀጋየ ገብረመድህን እንዳለው «ሞኞች» ነን።

እኔም እንደሌላው ወደብ እንደሚያስፈልገን ይገባኛል። ስለፈለግነው ብቻ ግን እንዲሁ በጩኸት አይገኝም። ማግኘት ደግሞ እንደ መፈለግ ቀላል አይደለም። የፍላጎታችን ማግኛ ቁልፍ ያለው በኤርትራ ህዝብ እጅ ነው። የሚያስፈልገን ነገር ለመቀበል ተቀባይ ሳይሆን አቀባይ/ሰጪ ጭምር መኖር አለበት። አሁን የምናየው አስቂኝ ውይይት፣ የፈላጊና ፈላጊ ትርጉም የለሽ ውይይት ነው። እንዲያው ለነገሩ እነዚህ በአሰብ ዙርያ የሚነታረኩ ሞኞች፤ «በሉ እንካችሁ አሰብ» ቢባሉ፣ ርክክቡን በየትኛው ቤተመንግሥት ሆነው ያስፈጽማሉ። ባገራቸው ቤተመንግሥት ያለው ወያኔ እንደሆነ፣ ለትግራይ የማይጠቅመውን አሰብ ሲል፣ ለዋሽንግተን ዲ.ሲ. አርበኞች ቤተመንግሥቱን የሚለቅ አይደለም። ነገሩ ሁሉ የልጅ ጨዋታ ነው። የአየር ባየር ጨዋታ።

ውይይት የሚሰጠው ጥቅም ካለ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ልጆች በአንድ መአድ ተቀምጠው በመከባበር የሚያደርጉት ውይይት ብቻ ነው። ከኤርትራዊያን ወገኖቻችን የምንወያየው ደግሞ ለኛ ጥቅም ብቻ ስንል አይደለም። ለነሱም ጥቅም፣ ለጋራ ለዘላቂና ለአስተማማኝ ጥቅም ሲባል ጭምር ነው። ሁለቱም ወገኖች አንዱ የሌላውን ችግር የሚፈቱበት ቁልፍ አላቸው። ሁለቱንም ቁልፎች አቅልጠን አንድ አስተማማኝና ሁሉንም የሚከፍት ጠቃሚ ቁልፍ (master key) ካልሠራን፣ የተጠናወተን በሽታ መድኃኒቱን ሳናገኝለት አመንምኖ ይፈጀናል። የጋራ በሽታችንን በጋራ ሐኪም አማካኝነት መድሃኒቱን ከመፈለግ በቀር ሌላ አማራጭም የለንም።

የኤርትራ ህዝብ ለዚህ ፍቱን መድሃኒት የጋራ ፍለጋ ያለውን ዝግጁነት በሙሉ እምነት ለማረጋገጥ እችላለሁ። ካሁን ወዲያ በኢትዮጵያ ህዝብ ከተተፋው ወያኔ ጋር በመወያየት የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝብ ተፈቃቅዶ በሰላም ይኖራል ብሎ የሚጠብቅ ኤርትራዊ እንደሌለ ገሃድ የወጣ ሃቅ ስለሆነ፣ ወያኔ ላልሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የውይይት መድረኩ ክፍት ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያኖች በእጃችን ያለውን ዳቦ ሳንበላ፣ የሚቦካ ዱቄት እንኳ ሳይኖረን፣ ሌላ ዳቦ ለመጋገር ስንባክን እንገኛለን። ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያዊ እውቀት አግኝቷል። ጥበብን (wisdom) ግን ገና አላገኛትም። በእውቀትና በጥበብ መካከል ብዙ ልዩነት አለ። እውቀት በጥበብ ካልታገዘ ደግሞ ብቻውን ጥቅም አይሰጥም። አንድ የሃይማኖት መሪ በእውቀትና በጥበብ መካከል ያለውን ግኑኝነት እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል። «አንድ ሰው፣ በቅዱስ ቁርዓን ወይም በአዲስና በብሉይ ኪዳን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ

ገፅ የሰፈሩትን ትእዛዛትና ህጎች ጠንቅቆና ተንትኖ ቢያውቅ፣ አዋቂ ሊባል ይችላል። የጥበብ ባለቤት የሚሆነው ግን፣ ከቅዱሳን መጻሕፍት ለቀሰማቸው ህግጋትና ትእዛዛት ተገዢ ሆኖ በተግባር ሲፈፅማቸው ብቻ ነው» ይላሉ። ትንሽ ጥበብ የሚጠይቅ፣ ትልቅ ጉዳይ ለማካፈል ይፈቀድኝ።

ወያኔ፣ ለራሱ ጥቅም ሲል ከሰባ ሺ በላይ የሚሆኑ ኤርትራዊያን (አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያዊያን ነን ብለው የሚያምኑ) ዘርፎና አዋርዶ ከኢትዮጵያ እንዳባረረ ይታወቃል። በቅርቡ ደግሞ ወያኔ ለነፃነቷ የተዋደቀላትን ኤርትራ ሲወር፣ ጥቃቱን ያነጣጠረው በወታደራዊ ተቋማት ላይ ሳይሆን፣ ምንም ሓጢአት በሌለው ሰላማዊው የኤርትራ ህዝብ ላይ ነው። ዛሬ ከአንድ ሚልዮን በላይ የሆነ የኤርትራ ህዝብ፣ ከቤት ንብረቱ ተፈናቅሎ በመጠለያ ስፍራዎች ይገኛል። በኤርትራ ህዝብ ላይ ለደረሰው ችግር ተጠያቂው ግፈኛው ወያኔ ቢሆንም፣ ድርጊቱን በሰብአዊ ርህራሄ ሳናወግዘው ብናልፍ፣ በዘለቄታው የኤርትራ ህዝብ እኛንም ወያኔ በሚያይበት ዓይን ተመልክቶ ቢያዝንብን አይፈረድበትም።

ለኢትጵያና ለህዝቧ የዘለቄታ ጥቅምና ዋስትና የምናስብ ከሆነና ጥበበኞች ከሆንን፣ ዛሬ በተፈናቃይ ኤርትራዊያን ወገኖቻችን መሃል ተገኝተን፣ ሃዘናችን ገልፀን፣ ብንቆረቆርለት የምንጎናፀፈው ፀጋ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል። ዛሬ የምንገኝበት መድረክ፣ ኢትዮጵያ ለሰላሳ ዓመታት በዘለቀው ጦርነት፣ በኤርትራ ላይ በመሬትና ባየር፣ እሳት የረጨችው፣ የኤርትራ ወደቦች ስለፈለገች ብቻ ነው? ወይስ ከወደቡ ጋር በኤርትራ የሚኖረውንም የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነውን ክቡር ሰው ፍለጋ ጭምር ነው? የሚለውን ጥያቄ መልስ ልንሰጥበት የምንገደድበት መድረክ ብቻ ሳይሆን፣ የምንከሰስበት ወሳኝ መድረክ ነው። ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ካልመለስን ደግሞ፣ የምናፍርበትና የምንሳቀቅበት ቀን ሩቅ እንዳልሆነ ለመረዳት ነብይ መሆን አያስፈልገንም።

ለኤርትራ ህዝብ መቆርቆር የሚገባን መሆኑን የማስገነዝበውን ያህል፣ በኤርትራ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎቻችንም ልናደርገው የሚገባን ጭምር ለማውሳት እወዳለሁ። በዚህ ዓመት ኤርትራን በጎበኘሁበት ወቅት የተመለከትኩትን ልመስክር።

ከሰባ ሺ በላይ ሰላማዊ የኤርትራ ዜጎችና በኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ለመቀጠል የመረጡ የኤርትራ ተወላጆች፣ በወያኔ አረመኔያዊ እርምጃ ተዘርፈውና ተጎሳቁለው ከኢትዮጵያ የተባረሩ ሰዎች በሚገኙባት ኤርትራ፣ ከመቶ ሺ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን፣ በኤርትራ ህዝብ ተከብረው ሲኖሩ በቅርብ ተመልክቻለሁ። ከብዙ አብነቶች ውስጥ አንድ እጅግ ያስደነቀኝንና ያስደስደሰተኝን ነገር ላካፍል።

ከኢትዮጵያ በግፍ ተዘርፈው ከተባረሩ የኤርትራ ተወላጆች አንዱ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የኬክና ብስኩት ጣፋጭ ምግቦች በማቅረብ ታዋቂ የሆኑት አቶ ገብረ ትንሳኤ ናቸው። አቶ ገብረ ትንሳኤ አሁንም በአስመራ ከተማ፣ ትንሽ ብትሆንም፣ በጣም የምታምርና አዲስ አበባ ቀመስ የሆንነው የምንገናኝባት ድንቅ የጣፋጭ ምግቦችና የቡና/ሻይ መሸጫ ንግድ ቤት አለቻቸው።

በዚች የንግድ ቤት፣ እኚሁ አዛውንት ሰው፣ አስራ ሦስት ሠራተኞች ቀጥረው ያስተዳድራሉ። ከነዚሁ ሠራተኞች ውስጥ አስራ አንዱ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ናቸው። ከሠራተኞቻቸው መሃል አንዱ (የትግራይ ተወላጅ) ቡና ይጋብዘኝና በጨዋታችን መሃል «ወደዚህ መምጣታችሁ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ዋስትና ነው» አለኝ። እኔም «የኔና ያንተ ዘመዶች ዘርፈው ካገር ያባረርዋቸው አቶ ገብረ ትንሳኤ ለናንተ ሥራ መስጠታቸው እንዴት ትመለከተዋለህ?» ስል ጠየቅሁት። ኢትዮጵያዊው ወንድሜ የሰጠው መልስ፣ «ወያኔ እዚህ በምንኖረው ኢትዮጵያዊያን አንገት ዙርያ ገመድ ነው የጠመጠመብን። አቶ ገብረ ትንሳኤ ግን፣ ብዙ የቀለም ትምህርት ባይኖራቸውም፣ ከህይወትና ከእድሜ ፀጋ ብዙ የተማሩ አዋቂ ሰው ናቸው።» የሚል ነበር።

በአንጻሩ ደግሞ፣ በጣም የገረመኝና ያሳዘነኝ፣ አንዳንድ ወያኔ ያሰማራቸው የትግራይ ተወላጅ ወጣቶች፣ የኤርትራ መንግሥት በሰላማዊ ኢትዮጵያዊያን ላይ የወያኔን እርምጃ እንዲደግም ግፊት (provoke) ለማድረግ፣ በህብረተሰቡ መሃል ረብሻ ሲፈጥሩ ማየቴ ነው። ከዚህ የተነሳ፣ በቅርቡ ከተካሄደው የወያኔ ወረራ በኋላ፣ የኤርትራ ህዝብና መንግሥት ትዕግስት ተሟጦ፣ በተወሰኑ ኢትዮጵያዊያን ላይ አንዳንድ ችግር ቢከሰት ብዙ አያስገርመኝም። በጣም ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ቢኖር፣ በአንዳንድ የወያኔ ቅጥረኞች ሰበብ፣ «ለሃጢያተኞች የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል» እንደሚባለው፣ በሌሎች ሰላማዊና ፀረ ወያኔ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ላይ በስህተት ችግር እንዳይደርስ፣ የሚመለከታቸው ሁሉ

ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ነው። በዚህ ረገድ፣ ይህ የዜጎች ጉዳይ በወያኔ መሰሪ ተግባር ለተጎዳው የኤርትራ ህዝብና መንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን፣ በውጭ የምንገኘው ኢትዮጵያዊያን ልንከታተለው የሚገባ ከፍተኛ ጉዳይ ነው። የጉዳዩን አሳሳቢነት ላብራራ።

በግጭቱ ምክንያት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ዜጎች በተለይ የትግራይ ተወላጆች፣ ይብዛም ይነስም ከወያኔም ይሁን ከሌላ ምንጭ የሚደጎሙበት መንገድ አለ። በኤርትራ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ግን አለሁላችሁ የሚልላቸው ወገን የሌላቸው፣ አውላላ ሜዳ ላይ የቀሩ ፍጡሮች ናቸው። የኤርትራ መንግሥት ብቻውን ሊያደርገው የሚችል ነገር ቢኖር በጣም ትንሽ ነው። ሌሎች  እርዳታ ለጋሾች እርዳታ እንዲያደርጉ ቢፈለግም፣ ጉዳዩ የኔ ነው ብሎ የሚከታተል የራስ ሰው ያስፈልጋል። ስለዚህ ከወደብ በፊት፣ ለኛ ጠቃሚው፣ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ መሆኑን ተገንዝበን፣ ወደብ አግኝተን በመርከብ እስክናንሸራሽረው ድረስ፣ ህዝባችን በርሃብ እንዳያልቅብን ባስቸኳይ ልንደርስለት ይገባል። እግረ መንገዳችንም፣ በጠላታችን ወያኔ የተፈናቀለውን ኤርትራዊ ወገናችን ዘንድ ደርሰን፣ ሃዘናችንና አክብሮታችንን ብንገልጽለት ለአገራችን ትልቅ ውለታ ማድረጋችን እንደሆነ፣ ልናጤነው የሚገባ ከፍተኛ ጉዳያችን ነው። ወደብ ማለትም ይህ ነው።

የአቶ ገብረ ትንሳኤ ሠራተኛ ሰውየውን «አዋቂ» ብሏቸዋል። እኔ ግን ለአቶ ገብረ ትንሳኤ የምሰጠው የቅፅል ስም «ጥበበኛ» የሚል ነው። የአዛውንቱ ግብረ ገብነትና ጥበብ ጠቄሜታው ለሰውየውና ለሠራተኞቹ ሳይሆን፣ ለኢትዮጵያዊያንና ለኤርትራዊያን በሙሉ ነው። እኛ ግን፣ በፈረንጅ ትምህርት አብደን፣ አፍሪካዊ፣ እስላማዊ፣ ክርስትያናዊና ባጠቃላይ ሰብአዊ ጥበብ ርቆን፣ እርስ በርሳችንም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር እንዳንደማመጥ፣ ሰይጣናዊ መንፈስ ተጠናውቶን፣ በዚህም አምላክ ተቆጥቶን፣ ወያኔ በተባለ ተስቦ በሽታ እየማቀቅን እንገኛለን። ፖለቲከኞችንና ህዝብን ለይተን ለማየት እንዳንችል፣ እርኩስ መንፈስ ልቦናችንን ሰልቦ፣ በአምላክ አምሳያ ስለተፈጠረው ክቡር ሰው መቆርቆር ትተን፣ ስለ ግኡዝ ወደብ ስንቀባጥር፣ ወርቅ በሆነው የህዝባችን ህይወትና ጊዜ በመቀለድ ላይ እንገኛለን።

አንዳንድ ኢትዮጵያዊያኖች፣ ሁሉም ትግሬ ወያኔ ነው፤ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ሁሉም ትግሬ የወያኔ ቫይረስ ተሸካሚ ነው ብለው ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ አብረናቸው በመቁሰል ላይ ባለነውም እየዘመቱ፣ «ከወንድሞቻችን» ከወያኔዎቹ ጋር ሊያስታርቁን ይሞክራሉ። የዚሁ ዘመቻ ሰለባ የሆኑ ብዙ ትግሮች አውቃለሁ። በተመሳሳይ መንገድ ሁሉም ኤርትራዊ ጠላት ነው የሚል ስሜት አላቸው። እነሱ እንደሚያስቡት፣ ሁሉም ኤርትራዊ ጠላት ከሆነ፣ ሁሉም ትግሬ ጠላት ከሆነ፣ ከባድ አደጋ ይጠብቃቸዋል ማለት ነው።  አገራችን ኢትዮጵያን ጨርሶ የሚበትናት ነገር ቢኖር፣ ይህ የተሳሳተ አመለካከት ብቻ ይሆናል። ድርጅትንና ህዝብን፣ መንግስትንና ህዝብን፣ ለይተን ማየት ይኖርብናል።

ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው፣ የሻዕቢያንና የወያኔን ግንኙነት ለመስበር ሲባል፣ ከመሰሎቼ ጋር ሆኘ ያልፈነቀልኩት ድንጋይ የለም። ይህም ሃቅ፣ ዛሬ ወደ አስመራ ስለምመላለስ፣ ለኤርትራ ህዝብም ሆነ መንግሥት የሚደበቅ ምስጢር አይደለም። ሻዕቢያን የተዋጋሁት ግን ኤርትራዊ በመሆኑ ወይም ለኤርትራ ጉዳይ በመታገሉ አይደለም። ሻዕቢያን አምርሬ የታገልኩት የወያኔ አጋር በመሆኑ ብቻ ነው። በራሱ «ቅዱስ መጽሐፍ» የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ለኤርትራና ለትግራይ ሰጥቶ፣ ለሌላው የከለከለን ወያኔ የሚደግፍ ማንንም ኃይል ልንቃወም የግድ ነው። በተረፈ፣ ራሳችን ኢትዮጵያዊያን ያበላሸነውን የኤርትራ ጉዳይ ምክንያት በማድረግ ከታገለ ኤርትራዊም ይሁን ድርጅት ጋር የግል ጠብ የለኝም።

የኤርትራ ጉዳይ የት ላይ እንደተበላሸና በኤርትራ ትግል እንዴት እንደተጀመረ ለመረዳት፣ የኤርትራን ፋይል እንደገና ከፍተን እንድንመረምር ወቅቱ ያስገድደናል። በቅርቡ ታትሞ የወጣው «በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የኤርትራ ጉዳይ» የተሰኘው የክቡር አቶ ዘውዴ ረታ መጽሐፍ፤ እጅግ የሚደነቅና ብዙ የተደከመበት ታላቅ የሥራ ውጤት  ነው። በመጽሐፉ ይዘት ላይ አንዳንድ የሚያወያዩ ነጥቦች ቢኖሩም ቅሉ፣ የኛ ትውልድ የኤርትራን ጉዳይ ምንነት በጥልቀት ለመመርመር እንዲችል፣ እኚህ ትጉህና ክቡር ዜጋችን፣ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ አስረክበውናል።

ለብዙ ዘመናት በቅርብ የማውቃቸውና፣ በኤርትራ ጉዳይ ከማንም የበለጠ እውቀት የነበራቸው እጅግ የምወዳቸው አባቴ፣ ክቡር ቢትወደድ አስፍሃ ወልደ ሚካኤል ከማለፋቸው በፊት፣ የኤርትራ ጉዳይ የተበላሸበትን ታሪክ ለትውልድ በጽሁፍ እንዲያስተላልፉ ስለምናቸው ነበር። ክቡርነታቸው በጤናና በሌሎችም ምክንያቶች

ራሳቸው በመጽሃፍ መልክ ባያቀርቡትም፣ ወደሚቀጥለው ዓለም በክብር ከመሄዳቸው በፊት፣ የክቡር አቶ ዘውዴ አድካሚ ጥረት ተባባሪና የሚታመን ምንጭ ሆነው የሥራው ተካፋይ መሆናቸው እጅግ ስላረካኝ፣ ዘውዴ ረታን የመሰለ ታታሪ ዜጋ የለገሰን ቅዱስ አምላክ የተመሰገነ ይሁን እላለሁ።

ክቡር አቶ ዘውዴ ረታ፣ እንደ ሌላው በስማ በለው ሳይሆን፣ የኤርትራውን ነገር አጨማልቀን ከትቢያ ጋር ስንቀላቅለው፣ እዚያው እቦታው ላይ ቆመው ለመታዘብ የታደሉ የእድሜ ባለፀጋ ናቸው። በተጨማሪም፣ ክቡርነታቸው ሥራው የሚጠይቀውን እውቀት በሙሉ አምላክ ያደላቸው ትጉህ ዜጋ ስለሆኑ፣ ይህንን መጽሐፍ በተለይ ብዙ ሰው ሊረዳው በሚችል በአማርኛ ቋንቋ ለትውልድ በማውረሳቸው፣ ለኛና በተለይም ለኢትዮጵያዊነት ሲል ደሙን አፍስሶና «ኢትዮጵያ ወይ ሞት» ብሎ <u>ኢትዮጵያና ሞት</u> አንድ ላይ ለተሰጠው ያልታደለው የኤርትራ ህዝብ ታላቅ ባለ ውለታ ናቸው።

ሁሌም እንደጻፍኩትና በደርጉ ዘመን በዜና ማሰራጫዎች ደጋግሜ እንደተናገርኩት፣ የኤርትራ ጉዳይ በአስከፊ ሆኔታ የተበላሸው፣ ፌዴሬሽኑ እንደፈረሰ ነው። ፌዴሬሽኑ በኤርትራ ህዝብ ፈቃድና ውክልና ይምጣ ይፍረስ ሌላ ራሱን የቻለ ውይይት ስለሚያሻው፣ አሁን ማንሳቱ አስፈላጊ አይደለም። እኔ የምከፍተው ፋይል፣ በአንድነት ታጋዮች ብርታት ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ፣ የተሠራውን በታኝ ተግባር በመኮነን፣ የኤርትራ ህዝብ በኛ በኢትዮጵያዊያን ላይ እምነት እንዲያጣ ያደረገውን የታሪካችን ንኡስ ፋይል ነው።

ከዚሁ አንጻር፣ የኛው የቡራ ከረዩ ድንፋታና የኤርትራዊያኑ ብሶት ምንነት፣ በትንሹም ቢሆን፣ ጨልፈን ለመታዘብ ያህል፣ ከክቡር አቶ ዘውዴ ረታ መጽሐፍ ልጥቀስ:-

> «ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ እጅግ የደከሙትና ውጤቱን ያስገኙት በተለይ ቢትወደድ አስፍሃና መላከሠላም ዲሚጥሮስ፤ ሚስዮናቸውን የፈጸሙ ስለሆነ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ከኤርትራ መውጣት አለባቸው። …ጥር 20 ቀን 1963 ዓ.ም. ዤኔራል ዐብይ አበበ፤ የመጀመሪያው የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ እንዲሆኑ፣ በጃንሆይ ከተነገራቸው በኋላ፤
>
> - ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል የፍርድ ሚኒስትር፣
> - መላከሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማሪያም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል፣ ሆነው መሾማቸው ከአስመራ ቤተመንግሥት መግለጫ ተሰጠ።
>
> ከዚህ በላይ እንደታየው የፌዴሬሽኑን መፍረስ ላከናወኑት ሰዎች የሥራ ድልድል ከተደረገ ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ፤ ለሚቀጥሉት ሁለት ሰዎች ንጉሠ ነገሥቱ የሰጡት ሹመት፤ መላ የማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባሎችን ከመጠን በላይ አሳዘነ።
>
> 1. በዚያ በትግሉ ዘመን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የለባትም ብለው ይቃወሙ የነበሩት፤ ፊታውራሪ ተስፋዮሐንስ በርሄ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ <u>የጠቅላይ ግዛቱ ምክትል እንደራሴ፣</u>
>
> 2. የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ ወገን ሆነው የአንድነቶች ተቃዋሚ የነበሩትና፣ ኋላም የምዕራባዊ ቆላ አውራጃ ከሌላው የኤርትራ ግዛት ተገንጥሎ፣ ነፃነቱን እንዲያገኝ ሲጥሩ የቆዩት አሊ ሙሳ ራዳይ፤ በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ፣ <u>የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ አማካሪ</u> ሆነው ተሾሙ።

‹ኢትዮጵያ ወይ ሞት› ብለው፣ ያንን ሁሉ መስዋዕትነት የተቀበሉት የአንድነት ወገኖች፣ እነሱ እንደተመኙትና እንደደከሙበት ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ውህደቱ ሲጀምር፣ አስተዳዳሪዎቻቸው ሆነው የሥልጣኑን ልጓም የሚጨብጡት፣ በህይወታቸው ላይ የፈረዱባቸው ባላጋራዎቻቸው ሲሆኑ፣ ለምን አያዝኑም? ለምንስ አይማረሩም? አንድነቶች አላማቸውን ከግቡ ለማድረስ በሚታገሉበት ዘመን፣ በባዕድ አስተዳዳሪዎች እየተጨቆኑ፣ ያለምክንያት ከሥራ እየተባረሩ፣ ያለ ጥፋት እየታሰሩ፣ ያንን ሁሉ የግፍ

በደል ሲቀበሉ፣ ራቢጣዎች የውጭ ጠላት በሚያፈስላቸው ገንዘብ ሕይወታቸውን በማንደላቀቅ ያሳለፉ ናቸው።

ኢትዮጵያዊነታችን ከተመለሰልን፣ በአገራችን ኮርተን በነፃነታችን ተከብረን እንኖራለን። ኢትዮጵያዊነታችንን ከተከለከልን ግን፣ እንዳለፉት ዘመናት የኮሎኒያሊስቶች መጫወቻ ከምንሆን፤ ሞትን እንመርጣለን ብለው፤ ቆርጠው የተነሱትና ሞትን የተጋፈጡት የአንድነት ሕዝቦች፤ በመጨረሻው የሚጠብቃቸው ዕድል፣ በባላጋራዎቻቸው ሥልጣን ሥር መውደቅ መሆኑን ቢያውቁት ኖሮ፤ ለኢትዮጵያ ወይ ሞት ያን ሁሉ መከራ ለመቀበል ባልሞከሩት ነበር። ኤርትራ ወደ እናቷ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ መስዋዕትነትን የተቀበሉ፣ በፌዴሬሽን የተደረገው ቅልቅል በአንዲት ኢትዮጵያ አስተዳደር እንዲለወጥ፣ ታግለው ድሉን ያገኙት አንድነቶች ብቻ መሆናቸው እየታወቀ፣ ሹመትና ሥልጣን ለራቢጣዎቹ ማሸከም ለምን እንዳስፈለገ፣ የሚያስረዳ አልተገኘም።

አንድነቶች በዚህ በተፈጸመባቸው በደል እጅግ አዝነው፣ እንደጎርፍ የወረደው እንባቸው፣ ቀስ በቀስ የኢትዮጵያዊት ኤርትራን የአንድነት ግንብ እያራሰ ለማፍረስ እንደሚያበቃው አርቆ ያሰበ የለም።...»

(የኤርትራ ጉዳይ በቀ. ኃ. ሥላሴ ዘመነ መንግሥት) ከዘውዴ ረታ፤ ገጽ፤ 513-514

ከክቡር አቶ ዘውዴ መጽሐፍ የጄኔራል ተድላ ዑቅቢት አሳዛኝ አሟሟትን ጨምሮ ብዙ ነገር ብጠቅስ በወደድሁ ነበር። ጊዜ ስለሚወስድ፣ ኢትዮጵያዊያን መጽሐፉን ፈልገው እንዲያነቡ መጋበዙ ይቀለኛል። በአቶ ዘውዴ መጽሐፍ በገጽ 520 እንደተመለከተው፤ በተደረገው መጥፎ ነገር አንጀታቸው በግኖ ዤኔራል ተድላ ዕቁቢት <u>«እኛ ነን እንጂ አገሬ፣ አንድነቴ፣ ወገኔ፣ ስንል የነበርን፤ እነሱማ (አማሮች) ወንበሬ የግዛት ወንበሬ በማለት ላይ እንደነበሩ</u> አሳዩን አለኝ» (ስርዝ የደራሲው ነው፤) የሚለውን ስመለከት ዛሬም ቢሆን <u>ወገኔ</u> የሚል ሳይሆን <u>አሰብ ወደቤ</u> ብቻ መባሉን ታሪክ ራሱን እየደገመ መሆኑን አስታወሰኝ።

እንግዴህ ይህ የአቶ ዘውዴ መጽሐፍ የነገረን ታሪክ ፌዴሬሽን እስከፈረሰበት ቀን ድረስ ያለውን አበሳ ነው። ከዚያ በኋላ እኛ ኢትዮጵያዊያን ያካሄድነው ሁሉ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ደግሞ፣ አቶ ዘውዴ ካቆሙበት ተነስቶ ብዙ የሚጻፍ ጉድ አለ። ይህን ሁሉ የማነሳው «ሁሉም ኤርትራዊ ጠላታችን ነው» የሚለውን እርኩስ አመለካከት የራስን የታሪክ ስህተትና ጉድለት ካለመገንዘብ የሚመነጭ መሆኑን ለማመልከት ነው።

በየስደቱ የሚኖሩ አንዳንድ ኤርትራዊያን፣ በደረሰው ሁሉ (በተለይ በምንከደው ሃቅ) ምክንያትና ከየዋህነትም የተነሳ፣ አንዳንድ አላስፈላጊ ቃላቶች ይሰነዝሩ ይሆናል። እነዚህ ግን የኤርትራን ህዝብ ቀርቶ ራሳቸውንም በሚገባ መወከላቸው እጠራጠራለሁ። የነዚሁ ዓይነት ከሁሉም ዘር አሉ። ከኔው ዘር ከትግሮቹ መካከልም፣ ከነሱ በቀር ሌላ አርበኛ የሌለ የሚመስላቸው የፈረንጅ አገር አርበኞች አልታጡም። እነዚህ ግን፣ ሁሉም ነገር ተስተካክሎ፣ ወደ አገር ቤት ተመልሰን አገር እንገንባ ቢባሉ መልከስከስ ከለመዱበት የፈረንጅ መንደር የማይነቃነቁ፣ ሁሌም ከአሸነፈው ጋር አለንልህ የሚሉ ናቸው። ስለዚህ፣ በየመሸታ ቤቱ በሚያላዝኑ መንገደኞች ሰበብ፣ በሚልዮን የሚቆጠረውን የገጠር ህዝብ እነደጠላት መቁጠር እጅግ የተሳሳተ አመለካከት ነው። በጦርነትም ሆነ በድርቅ፣ በሌላውም ችግር የሚጠበሰው ደግሞ እነዚሁ አውደልዳዮች ሳይሆኑ፣ ከምኑም የሌለው ሰፊውን ህዝብ መሆኑን ማጤን ይገባናል።

ጽሁፌን የምቋጨው፣ ለበሽታችን መድኃኒቱም ሆነ፣ በሽታው ተመልሶ እንዳያውከን፣ ለአንዴና ለመጨረሻ እንድናጠፋው ከተፈለገ፣ <u>ከኤርትራ ህዝብ ጋር አብረን ስንሠራና ስንመክር ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ ነው።</u>

ሰላምና ብልጽግና ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝብ ለዘለዓለም ይሁን።

ጥቅምት 1993 * November 2000

<u>ወደ ፊጣን ቤት ለመመለስ</u>